# የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ስለመጀመር?

ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ ትምህርት መጀመር ለህጻናት፥ ለወላጆችና ለተንከባካቢዎች ኣስደሳች ጊዜ ነው።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያው ዓመት ፋውንዴሽን ወይም የዝግጅት ጊዜ (Prep) ይባላል።

በቪክቶሪያ የመንግሥት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ልጅዎን ለማስመዝገብ ልጅዎ ትምህርት ከሚጀምርበት አመት ከአንድ ዓመት በፊት እነዚህን ተግባራት ያከናውኑ።

## ማመልከቻውን ከመሙላትዎ በፊት

በድረ ገጻችን ላይ መቼ እና እንዴት እንደሚመዘገብ ያንብቡ

ልጅዎ ትምህርት ለመጀመር ትክክለኛው እድሜ ላይ እንደሆነ ያረጋግጡ

የእርስዎን የመኖሪያ አካባቢ ያግኙ ትምህርት ቤት እና ሌሎች በአቅራቢያው በሚገኙ የመንግሥት ትምህርት ቤቶችን ለማግኝት የሚከተለውን ድረገጽ ይጎብኙ **findmyschool.vic.gov.au**

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በቀጦር ለመጎብኝት ወይም ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ

## ለፋውንዴሽን ምዝገባ ማመልከት

ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ የማመልከቻ ቅጽን ያግኙ

የሚያስፈልጉትን ሰነዶች ይሰብስቡ

ሁሉንም ነገር በወቅቱ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያስገቡ (ባሉበት አመት የጁላይ (ሐምሌ) ወር የመጨረሻው ዓርብ)

ትምህርት ቤቱ እስኪያነጋግርዎት ድረስ ይጠብቁ (ይህ የሚሆነው በነሐሴ/August የመጀመሪያ 2 ሳምንታት ውስጥ ነው)

**ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እና የተተረጎሙ ሰነዶች ላይ ለመድረስ፡**

ምዝገባ በማድረግ
ፋውንዴሽን ጀማሪ (Prep) |
የቪክቶሪያ መንግሥት

THE EDUCATION STATE

VICTORIA State Government | Department of Education

23-082